የሰ/መ/ቁ. 44235

መጋቢት 28 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- ቄስ ጌታቸው ተሾመ

**ተጠሪ**፡- ዓቃቤ ሕግ

**ፍ ር ድ**

አመልካች በስር ፍርድ ቤት በቀረበባቸው ሁለት የወንጀል ክሶች ጥፋተኛ ተብለው በሁለት አመትና በ300.00 ብር እንዲቀጡ የተሰጠው ውሳኔ የሕግ ስህተት አለበት በሚል ይህን የሰበር አቤቱታ ሊያቀርቡ ችለዋል፡፡

በሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አቃቤ ሕግ ባቀረበባቸው አንደኛ ክስ የወንጀል ሕግ ቁጥር 543/1/"ን" በመተላለፍ የካቲት 29 ቀን 2000 ዓ.ም ከቀኑ 5 ሰዓት ድርጊቱ ሞትን ሊያስከትል እንደሚችል ማሰብ ሲገባው ባለመጠንቀቅ የቡዳ መድሃኒት ነው ብሎ ቅጠላቅጠል አጨሶ በማጠንና ማረሻ አግሎ ከፊቷ ላይ በመተኮስ ሟችን የገደለ በመሆኑ በቸልተኛነት ሰው መግደል ወንጀል ተከሷል፣እንዲሁም በሁለተኛ ክስ ጉጂነቱ ጉዳቱ በተረጋገጠ ልማዳዊ ድርጊት የቡዳ መድሃኒት ነው ብሎ ቅጠላ ቅጠል አጨሶ በማጠን ማረሻ አግሎ ፊትዋን በተመተኮስ ለሞት ያበቃት በመሆኑ በልማዳዊ ድርጊት ጉዳት ማድረስ ወንጀል ተከሷል በማለት ክስ መስርቶባቸዋል፡፡ አመልካች ድርጊቱን አልፈፀምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም በማለታቸው አቃቤ ሕግ ሶስት የሰው ምስክሮች አቅርቦ አሰምቷል፡፡ ፍ/ቤቱም የአቃቤ ሕግ ምስክሮች እንደክስ አቀራረቡ አስረድተዋል በማለት አመልካች ክሱን እንዲከላከሉ በማለቱ አመልካች ድርጊቱ ተፈፀመ በተባለበት እለት ሟች ቤት ያልነበሩ ስለመሆናቸው ይመሰክሩልናል ያሏቸውን ሁለት ምስክሮች አቅርበው አሰምተዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ማስረጃ ከመረመረ በኋላ የአመልካች ምስክሮች ቃል እርስ በእርሱ የሚጋጭና የአቃቤ ሕግ ምስክሮች ያስረዱትን ለማስተባበል ያልቻለ ነው በማለት በሁለቱም ክሶች አመልካችን ጥፋተኛ በማለት በአንደኛው ክስ ሁለት አመት ቀላል እስራት በሁለተኛው ክስ 300.00(ሶስት መቶ ብር) እዲቀጡ ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ላይ ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ቢያቀርቡም ይግባኙ ተቀባይነት ያላገኘ ሲሆን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታም አቅርበው ችሎቱ በአብላጫ ድምጽ ውሳኔው መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት መዝገቡን ዘግቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ሲሆን አመልካች በቅሬታቸው ጥፋቱን ለመፈፀማቸው ከጥርጣሬ በላይ የተረጋገጠባቸው መሆኑን፣ሟች ቀድሞውኑ ታማ ስለነበር ለሞቷ ምክንያት የሆነው የያዛት ህመም መሆኑን፣ባትታመም ኖሮ ቅጠሉ ወይም ማረሻው ጉዳት ያደርስ እንደሆነ እንጂ ለሞት የማያበቃት

መሆኑን፣ቅጠሉ ሰው ገዳይ ለመሆኑ በህክምና አለመረጋገጡን እንዲሁ በተደራራቢ ክስ መከሰሳቸው አግባብ አለመሆኑን በመዘርዝር የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሳኔው እንዲሻር ይህ የሚታለፍ ከሆነ ደግሞ በወ/ሕ/ቁ. 567 ብቻ ተጠያቂ እንዲሆኑ ጠይቀዋል፡፡ ይህ ችሎት አመልካች በወ/ሕ/ቁ. 543 እና 567 መሰረት መከሰሳቸው በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለቱ የግራ ቀኙ የቃል ክርክር ተሰምቷል፡፡

ከፍ ሲል እንደተመለከትነው አመልካች የተከሰሱት በቸልተኛነት ሰው ገድለዋል እንዲሁም በልማዳዊ ድርጊት ጉዳት አድርሰዋል በማለት በሁለት የወንጀል ድርጊቶች ነው፡፡ አመልካችም በሁለት ተደራራቢ ወንጀሎች ልጠየቅ አይገባም በማለት የሚከራከሩ ሲሆን ተጠሪም በቃል ክርክር ወቅት አመልካች በተደራራቢ ወንጀሎት መከሰሳቸው አግባብ አልነበረም በማለት ገልጿል፡፡ ችሎቱም ተፈፀመ ከተባለው ድርጊት አኳያ አመልካች በተደራራቢ ወንጀሎች ጥፋተኛ ሊባሉ ይገባል ወይ የሚለው ጭብጥ መርምሯል፡፡ አመልካች በሁለቱም ክሶች ፈፀሙ የተባለው ሟችን የቡዳ መድሃኒት ነው ብለው ቅጠላ ቅጠል አጭሰው በማጠንና ማረሻ አግለው ፊትዋን በመተኮስ ለሞት ዳርገዋታል በማለት ነው፡፡ አመልካች በክሱ የተገለፀውን ድርጊት መፈፀማቸው ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ፈጽመዋል የተባለው ይኸው ድርጊትም በግል ተበዳዩዋ ላይ ጉዳት ማድረስ ብቻ ሳይሆን ሞትን በማስከተሉ ሁለት ክስ መቅረቡን ተገንዝበናል፡፡ ነገር ግን በሕግ በተጠበቀ በአንድ መብት ላይ የሚደረጉ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ የተቀላቀሉ የወንጀል ድርጊቶች የተደረጉት በአንድ የወንጀል ማድረግ ሃሳብ ወይም ቸልተኛነት ሲሆን እና ድርጊቶቹ በሙሉ በአንድ ድንጋጌ ሥር የሚሸፈኑ ሲሆኑ አድራጊው በተመሳሳይ ባህሪ ባላቸው በሁለት ወይም ከሁለት በበለጠ ተደራራቢ የቅጣት ድንጋጌዎች እንደማይቀጣ የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 61/1/ ያመለክታል፡፡ አመልካች መፈፀማቸው የተረጋገጠው የቡዳ መድሃኒት ነው በሚል ቅጠላ ቅጠል አጭሶ በማጠንና ማረሻ አግሎ በመተኮስ  የግል ተበዳይ ድርጊቱ ከተፈፀመ ከአንድ ሰአት በኂላ እንድትሞት ማድረጋቸው ነው፡፡ አመልካች በልማዳዊ ድርጊት ጉዳት ያደረሱና ጉዳቱም ሞትን ያስከተለ ቢሆንም ወንጀሉን የፈፀሙት በአንድ ቸልተኛነት ድርጊት በመሆኑ በተደራራቢ ቅጣት ሊቀጡ አይገባም፡፡ በሌላ በኩል በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 567 እንደተመለከተው ማንም ሰው ኢሰብአዊነቱ በታወቀና ጉጂነቱ በህክምና ሙያ በተረጋገጠ በልማዳዊ ድርጊት አማካኝነት በሌላ ሰው ላይ አካል ወይም አእምሮ ጉዳት ወይም ሞት እንዲደርስ ያደረገ ከሆነ በወንጀል ይቀጣል፡፡ በመሆኑም ምንም እንኳን አመልካች የፈጸሙት ጉጂ ልማዳዊ ድርጊት ሞትን ያስከተለ ቢሆንም ድርጊቶቹ በሙሉ ከፍ ሲል በተጠቀሰው ድንጋጌ ስር የሚሸፈን በመሆኑ አመልካች በቸልተኛነት ሰው በመግደል የወንጀል ድርጊት ሊቀጡ የሚገባበት የሕግ መሰረት የለውም፡፡ በመሆኑም አመልካች በወንጀል ሕግ ቁጥር 543 ጥፋተኛ መባላቸው መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት፡፡

በሌላ በኩል ግን የተፈፀመው ልማዳዊ ድርጊት ሞትን ያስከተለ ከሆነ እንደነገሩ ሁኔታ በአንቀጽ 561 ወይም 562 ከተመለከቱት ቅጣቶች አንዱ ተፈፃሚ እንደሚሆን የወንጀል ህጉ አንቀጽ 567 ያመለክታል፡፡ በዚህም መሰረት ወንጀል ሕጉን 561/2/ ስንመለከት የሞት አደጋ የተከሰተው በቸልተኛነት የሆነ እንደሆነ አንቀጽ 543 ተፈፃሚ ሊሆን እንደሚገባ ያመለክታል፡፡ በዚህም መሰረት አምልካች ከስድስት ወር እስከ ሶስት አመት ቀላል እስራት ወይም ከሁለት ሺህ ብር እስከ አራት ሺህ ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጫ ሊቀጡ እንደሚችሉ የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 543/1/ ያስገነዝበናል፡፡ አመልካች ጉዳት ሊያደርስ እንደሚችል እያወቁ ወይም ማወቅ ሲገባቸው በሕመም ላይ ያለን ሰው ቅጠል አጭሰው በማጠንና ማረሻ አግለው በመተኮስ ለሞት መዳረጋቸው ሲታይ ድርጊቱ አስከፊ መሆኑንና በሌላ በኩል ደግሞ አመልካቹ ያልተማሩና የ9 ቤተሰብ አስተዳዳሪ በመሆናቸው ቅጣቱን ሊያቀል የሚችል መሆኑ ከግምት ውስጥ በማስገባት የስር ፍ/ቤት አመልካችን በሁለት አመት ቀላል አስራት እንዲቀጡ የሰጠው የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የሰሜሽ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 19090 ግንቦት 19 ቀን 2000 ቀን ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ፣የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 6880 መስከረም 15 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ እንዲሁም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 00683 ታህሣስ 13 ቀን 2001 ዓ.ም በድምጽ ብልጫ የሰጠው ትእዛዝ ተሻሽሏል፡፡